# የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ

# (ብአዴን)

# በ7ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ተሻሽሎ የፀደቀ

# መተዳደሪያ ደንብ

*መስከረም 1999 ዓ.ም*

# የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)
# በ7ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ተሻሽሎ የፀደቀ
# መተዳደሪያ ደንብ

## መግቢያ

ድርጅታችን ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ብአዴን ባሳለፋቸው የትግል አመታት የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ የሚጠይቀውን የትግል አላማ፣ መስመሮች፣ ስልቶችና የአደረጃጀት አግባቦችን በመከተል ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡

በአገራችን ፋሽስታዊ ጽልመት ነግሶ በነበረበትና በህዝባዊ ትግሉ ጐራ ተሰልፎ የነበረው ኢህአፓ በተከተለው የተሳሳተ የትግል መስመርና በውስጡ በነበረው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አመራር ምክንያት በትግሉ መቀጠል ተስኖት በተፍረከረከበት ወቅት ያሁኑ ብ.አ.ዴ.ን የያኔው ኢ.ህ.ዴ.ን በህብረ-ብሔር ፕሮግራምና አደረጃጀት ትግሉን ቀጥሏል፡፡

በአገራችን ውስጥ ከአንድ ምእተ ዓመት በላይ ተንሰራፍቶ የቆየው ብሔራዊ አድልዎና አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና ከአምባገነኑ የደርግ መንግስት ውድቀት ጋር ዳግም በማይመለስበት ሁኔታ መወገዱ በአገራችን አዲስ ዘመን እንዲበሰር አድርጓል፡፡ በዚህ የብሄራዊ እኩልነት ዘመን ሁሉም የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች በአንድ በኩል ለብሄራቸው ህዝብ ጥቅም በሌላ በኩል ደግሞ ለሁሉም የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች የጋራ ተጠቃሚነት ለመታገል የቆረጡ ነባርና አዳዲስ ብሄራዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች በሰፊው መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ህብረ ብሄራዊው ኢህዴን ይጫወት የነበረውን ሚና የሚተኩ በርካታ ብሄራዊ ድርጅቶች በመፈጠራቸው ኢህዴን ራሱን ወደ ብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ብአዴን/ በመቀየር ለሰፊው የአማራ ህዝብ ተጠቃሚነት መንቀሳቀስ የጀመረበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

ብአዴን በአገራችን ውስጥ የሰላምና የዴሞክራሲ መድረክ ከተጀመረበትና ራሱን በብሔራዊ መልክ ካደራጀበት ጊዜ አንስቶ የአማራ ብሔርንና በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦችን በአብዮታዊ ዴሞክራሲዊ ፕሮግራም ዙሪያ ለማሰባሰብ ተንቀሳቅሷል፡፡ በክልላችን እንዲሁም በአገራችን ውስጥ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አላማዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የተመሰረቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገቶችን ለማምጣት በፅናት ታግሏል፡፡ አጥጋቢ ድሎችንም ተጐናጽፏል፡፡

ብአዴን የደርግን መንግሥት ለመገርሰስ በተካሄደው የትጥቅ ትግልም ሆነ ደርግ ከወደቀ በኋላ በነበሩበት ጊዜያት ውስጥ የህብረ-ብሔራዊው ግንባር ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ አንድ አካል በመሆን በአገሪቱ ውስጥ ለተመዘገቡት ፈርጀ ብዙ ለውጦች የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል:: የአማራ ህዝብ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች ጋር በእኩልነት ላይ በተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት እንዲተሳሰር፣ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድርና ብሔራዊ ጥቅሞቹን እንዲያስከብር የሚያስችሉት አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ተግባራትን አከናውኗል::

ብአዴን የሰራቸውን ሥራዎች፣ ያስገኛቸውን ውጤቶች በተገቢው ሚዛን እየለካ፣ ጉዞውን በየጊዜው እየገመገመ፣ ከጠንካራም ሆነ ደካማ ጐኖቹ ጠቃሚ ትምህርቶችን እየገበየ የሚሄድ ድርጅት ነው:: የደርግ መንግሥት ወድቆ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሀይላችን ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በነበሩት አሥር አመታት ውስጥ የነበረውን ጉዞም በመገምገም በድርጅቱ ውስጥ እያቆጠቆጠ መጥቶ የነበረውን የጥገኛ ዝቅጠት አደጋ ከሥሩ ለመንቀልና ድርጅታችንን ለማደስ ሰፊ የተሃድሶ እንቅስቃሴ አካሂዷል:: በተሃድሶው እንቅስቃሴ አማካኝነትም በድርጅታችን ውስጥ የነበሩትን የአመለካከት፣ የአሰራርና የአደረጃጀት ችግሮች መፍታት የምንችልባቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች መያዝ ተችሏል:: በተሃድሶ የጠሩ መስመሮችን መሰረት በማድረግ የድርጅታችን ፕሮግራም እንዲሻሻል፣ በአመራር፣ በአሰራርና በውስጠ-ድርጅት ዴሞክራሲ ... ወዘተ ዙሪያ የነበሩብንን ድክመቶች በሚያስወግድ አግባብ የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ ማዘጋጀት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል::

የብአዴን መተዳደሪያ ደንብ በድርጅቱ ውስጥ የሃሳብና የተግባር አንድነት እንዲኖር፣ ውስጠ-ድርጅት ዴሞክራሲ የድርጅቱ ህልውና መሰረት በመሆኑ ተጠብቆ እንዲቀጥል፣ በአባላትና በአመራሩ እንዲሁም በየደረጃው ባሉ የአመራር አካላት መካከል ዴሞክራሲያዊና መርህን የተከተለ ግንኙነት እንዲዳብር፣ የብዙሃን ተሳትፎ እንዲያድግ፣ የአባላት መብትና ግዴታዎች በአግባቡ እንዲከበሩ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲጐለብት የሚያደርግ የግንባታ መሳሪያ ነው::

መተዳደሪያ ደንባችን የድርጅታችን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሚገለጽበት፣ በፕሮግራማችን ዙሪያ በመሰባሰብ ለአላማችን መሳካት ለመታገል የተዘጋጁና ድርጅታችንን የሚቀላቀሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችን የምናሰባስብበት፣ አገር አቀፉን አብዮታዊ ዴምክራሲያዊ ተልእኮ በአማራ ብሔራዊ ክልል ለመተግበር ተደራጅተን የምንሰማራበት፣ በአገሪቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 46/1985 መሰረት ህጋዊ ሰውነት የሚረጋገጥበት መሰረታዊ ሰነድ ነው::

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀፅ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ "በብአዴን ሰባተኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ተሻሽሎ የፀደቀ የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) መተዳደሪያ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ 2

### የድርጅቱ መጠሪያ

የድርጅቱ መጠሪያ « የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)» ነው፡፡

### አንቀፅ 3

### የድርጅቱ አርማ

የድርጅቱ አርማ በግራና ቀኝ የስንዴ ዘለላና የፋብሪካ መዘውር ከስር የተሳሰሩበት፣ ከመሀል የአማራ ሰማእታት ሐውልትና ከሐውልቱ ግርጌ ሚዛንና መፅሀፍ፣ ከመዘውሩና ስንዴው የላይኛው ጫፍ መገናኛ ላይ ኮከብ ያለበት ነው፡፡

### አንቀፅ 4

### የአርማው ትርጉም

የድርጅቱ ዓርማ የሚከተለውን ትርጉም ይይዛል፡፡

4.1. ስንዴው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዋነኛ ማህበራዊ መሰረት የሆነውን አርሶ አደርና ገጠርንና ግብርናን ማእከል ያደረገውን የልማት ስትራቴጂያችንን ይወክላል፡፡

4.2. የፋብሪካ መዘውሩ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማህበራዊ መሰረት የሆነውን ላብ አደርና በከተማ የሚኖረውን ሰርቶ አደር እንዲሁም ቀጣዩን የአገራችንን ኢንዱስትሪያዊ እድገት ይወክላል፡፡

4.3. የአማራ ሰማእታት ሐውልት ለዴሞክራሲ፣ ለፍትህ፣ ለህዝቦች ብልፅግናና ለአገራችን ነፃነት መከበር ሲታገሉ የተሰው የአማራ ብሔርና በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች ልጆች ትግል ፍሬ ማፍራቱን ያመለክታል፡፡ በሌላም በኩል የአማራ ብሔር ህዝብ የትግልና የድል ታሪክ ምልክት ነው፡፡

4.4. ሚዛኑ ለፍትህ፣ ለሰላም፣ ለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር መስፈን በመካሄድ ላይ ያለውን ትግልና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት የሚደረገውን ርብርብ ይወክላል፡፡

4.5. መፅሐፉ አብዮታዊው ምሁር በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ያለውን የመሪነት ሚና ይወክላል።

4.6. ኮከቡ የበለፀገችና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የአማራ ክልል ህዝቦች ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር ያላቸው ፅኑ ወንድማማችነትና ትስስርን ያመለክታል።

## አንቀፅ 5

## የድርጅቱ ልሳን

5.1. የድርጅቱ ይፋ አቋሞች የኢህአዴግ ልሳን በሆነው በ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ላይ ይገለፃሉ።

5.2. እንደ አስፈላጊነቱ እየታየ ማእከላዊ ኮሚቴው ሌላ የድርጅት ልሳን ሊያደራጅ ይችላል።

## አንቀፅ 6

## የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት

የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት ባህር ዳር ነው። ድርጅቱ በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥና እንደ አስፈላጊነቱም ከክልሉ ውጭ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊከፍት ይችላል።

## አንቀፅ 7

## የፆታ አገላለፅ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በተባእታይ ፆታ አጠቃቀም የተገለፀው በሙሉ ለአንስታይ ፆታም የሚያገለግል ይሆናል።

## ምዕራፍ ሁለት

## አባልነት፣ የአባል መብትና ግዴታ

## አንቀጽ 8

## አባልነት

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በራሱ ፈቃድ የብአዴን አባል መሆን ይችላል።

8.1. የአማራ ብሔር ተወላጅ፣ በክልሉ የሚገኙ ብሔር ብሄረሰቦች ተወላጅ፣ ወይም የአማራ ክልል ነዋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ፣

8.2. እድሜው 18 ዓመት የሞላ፣

8.3. የብአዴንን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ፣ ለተግባራዊነቱ በፅናት የሚታገል፣ ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወትና መልካም ስነ-ምግባር ያለው፣

8.4. በድርጅቱ መመሪያ መሰረት ወርሀዊ መዋጮ ለመክፈል ዝግጁ የሆነ፣

8.5. በድርጅቱ መዋቅር በአንዱ ውስጥ ተደራጅቶ ለመንቀሳቀስ የተዘጋጀ፣

8.6. የፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን በህግ ያልተከለከለ፣

## አንቀፅ 9

## አባል ስለመመልመልና ማፅደቅ

### 9.1. ስለምልመላ፣

9.1.1. ማንኛውም የብአዴንን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ የሚቀበል ግለሰብ በአካባቢው ለሚገኝ የብአዴን አባል ወይም አካል የአባልነት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

9.1.2. በየአካባቢው የሚገኝ ማንኛውም የብአዴን አባልና አካል ለድርጅቱ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ታማኝ እንደሆነና በተግባራዊ የህዝብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ንቅናቄ በግንባር ቀደምነት እየታገለ ነው ብሎ ያመነበትን ግለሰብ ፈቃደኝነቱን አረጋግጦ ለድርጅት አባልነት መመልመል ይችላል፡፡

9.1.3. ተመልማዩን ግለሰብ የሚያቀርበው አባል ወይም አካል በአባላት መመልመያ ቅጽ መሰረት ሪፖርቱን በማዘጋጀት ከአስተያየት ጋር ለህዋሱ ያቀርባል፡፡

### 9.2. ስለ ዕጩ አባልነት

9.2.1. ማንኛውም የብአዴን አባል ለመሆን የተመለመለ ሰው ሙሉ የድርጅቱ አባል ከመሆኑ በፊት ለ6 ወር የእጩ አባልነት ጊዜ ማሳለፍ አለበት፡፡

9.2.2. በእጩነት ቆይታው ግለሰቡ ወደ ሙሉ አባልነት ለመሸጋገር መስፈርቱን በበቂ የማያሟላ ከሆነ የእጩ አባልነት ጊዜው እስከ 3 ወር ድረስ ሊራዘም ይችላል፡፡ የእጩ አባልነት ጊዜው እንዲራዘም ሲወሰን ከነምክንያቱ ለአባሉ ይገለጽለታል፡፡

9.2.3. የእጩ አባልነት ጊዜ ግለሰቡ የድርጅቱን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ተወያይቶ ከተቀበለበትና እጩ አባል እንዲሆን ከፀደቀበት ጊዜ ይጀምራል፡፡

### 9.3. አባልነትን ስለማጽደቅ

9.3.1. ግለሰብ አባላትን የመመልመል፣ እጩም ሆነ ሙሉ አባልነትን የማፅደቅ ሃላፊነትና ዝርዝር አፈፃፀም ማእከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

9.3.2. እጩም ሆነ ሙሉ አባልነቱ ሲፀድቅ የግል ማህደሩ ላይ እንዲሰፍርና ተመልማዩም እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

9.3.3. ማንኛውም እጩም ሆነ ሙሉ አባል እንደየደረጃው የድርጅት አባልነት መታወቂያ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

9.4. ስለ የክብር አባልነት

9.4.1. በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ የብአዴን አባል ሆኖ በብአዴን አደረጃጀቶች ውስጥ ተደራጅቶና የአባልነት ግዴታዎችን አሟልቶ ለመንቀሳቀስ የማይችል ነገር ግን የብአዴንን ኘሮግራም የሚቀበልና የድርጅቱ አስተማማኝ ደጋፊ ሆኖ የብአዴን አብዮታዊ ዓላማዎች እንዲሳኩና ህዝባዊ ተቀባይነት እንዲያገኙ ዓርአያነት ያለው ሚና የሚጫወት ግለሰብ የክብር አባል ሊሆን ይችላል፡፡

9.4.2. የክብር አባልነት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይፀድቃል፡፡

9.4.3. ተጨማሪ የአፈፃፀም መመሪያ በማእከላዊ ኮሚቴ ይወጣል፡፡

## አንቀፅ 10
## የአባላት መብቶች

10.1. ማንኛውም ሙሉ አባል በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በድርጅቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ደረጃዎች ለተለያዩ ተግባራት በሚደረጉ ምርጫዎች የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው፤ በድምፅ በሚወሰኑ ጉዳዮችም ላይ ድምፅ የመስጠት መብት አለው፡፡

10.2. የማንኛውም አባል የመናገርና የመፃፍ መብት የተከበረ ነው፡፡ በድርጅቱ ስብሰባዎች የመሳተፍ፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በህጋዊ መድረኮችና በፅሁፍ ሃሳቡን በነፃ የማራመድ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

10.3. በድርጅቱ ፕሮግራምና ስትራቴጂ እንዲሁም መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተለየ ወይም አዲስ ሃሳብ ያለው ማንኛውም አባል ሃሳቡን ወይም ልዩነቱን የማቅረብና የመከራከር፣ ያልተረዳው ጉዳይ ካለም ተገቢ ማብራሪያ የማግኘት መብት አለው፡፡

10.4. ማንኛውም ሙሉ አባል የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያዎች በሚፈቅዱት አግባብ ፖለቲካዊ ልዩነቱን ለመላው የድርጅቱ አባላት እንዲዘረጋለትና ድርጅት አቀፍ ውይይት እንዲደረግበት እንዲሁም አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

10.5. ማንኛውም የድርጅቱ አባል ስለራሱ፣ ስለአለበት አካል፣ ስለድርጅቱ አመራርም ሆነ በአጠቃላይ ስለድርጅቱ ማወቅ የሚገባውን ነገር እስከ ማእከላዊ ኮሚቴ ድረስ የመጠየቅና መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡

10.6. ማንኛውም አባል የኃላፊነት እርከን ሳያግደው እስከ ማእከላዊ ኮሚቴ ድረስ ሂስ የማቅረብና የሂሱንም መልስ የማግኘት መብት አለው።

10.7. ማንኛውም አባል ድርጅቱን በፍላጐት ይቀላቀላል። ባልፈለገበት ወቅት ደግሞ የመሰናበት መብት ይኖረዋል።

**10.8.** በእድሜ ወይም በጤና ችግር ምክንያት በድርጅቱ ውስጥ በንቃት መሳተፍ ያቃተው አባል በክብር የመሰናበትና የክብር አባል ሆኖ የመቀጠል መብት አለው። ዝርዝሩ ማእከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል።

10.9. ማንኛውም አባል ያለ በቂ ምክንያትና ያለ ህጋዊ አካል ውሳኔ ቅጣት አይወሰንበትም። ቅጣት ሲወሰንበትም የሚቀጣበትን ምክንያት በግልጽና በዝርዝር እንዲያውቀው ይደረጋል። የተሰጠው ቅጣትና ምክንያቱ እንዲሁም የአባሉ አስተያየት ከግል ማህደሩ ጋር ተያይዞ ይቀመጣል። በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለውም ይግባኝ የመጠየቅና ምላሽ የማግኘት መብት አለው። የቅጣቱ አወሳሰንና የይግባኝ ስርዓቱን በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ይወጣለታል።

**10.10.** ለሙሉ አባላት ተለይተው ከተቀመጡት ውጭ ያሉ መብቶች እጩ አባላትንም ይመለከታል።

## አንቀፅ 11

## የአባላት ግዴታዎች

**11.1.** እጩና ሙሉ አባላት ሁሉም ተመሳሳይ ግዴታዎች ይኖራቸዋል።

11.2. ማንኛውም አባል በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ ለብአዴን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ፖሊሲዎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች የመገዛትና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምነት የመታገል ግዴታ አለበት።

**11.3.** ማንኛውም አባል በተሰማራበት የስራ መስክ ሁሉ በተግባር ግንባር ቀደምና ውጤታማ መሆን፤ ተልእኮውን በቅንነትና በታማኝነት መፈፀም ይጠበቅበታል።

11.4. ማንኛውም አባል የብአዴንን ፕሮግራም፣ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎችን ወደ ብዙሃኑ ህዝብ የማስረጽና የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

**11.5.** ማንኛውም አባል የሰላም፣ የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደርና የልማት እንቅስቃሴን የሚያደናቅፉ አስተሳሰቦችንና ድርጊቶችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ መታገል ይኖርበታል።

11.6. ማንኛውም አባል ህብረተሰቡ በሚያካሄደው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ንቅናቄ ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው የወጡ ሀይሎችን የመለየትና በፈቃዳቸው የብአዴን አባል እንዲሆኑ የመመልመል ኃላፊነት አለበት፡፡

11.7. ማንኛውም አባል ለሰፊው የአማራ ህዝብ ማንነት መከበር፣ ለአማራ ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት መጠናከርና ለሰፊው ህዝብ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ጥቅምና ባህል መዳበር እንዲሁም ለዜጐች መብት መከበር እና ለመልካም አስተዳደር መስፈን የመታገል ግዴታ አለበት፡፡ ትምክህተኝነትና ጥገኝነትን በፅናት መታገል ይኖርበታል፡፡

11.8. በየደረጃው የሚኖሩ የብአዴን የአመራር አባላት የግል ሃብትና ንብረታቸውን እንዲሁም ቋሚ ገቢያቸውን ለድርጅቱ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙን በሚመለከት መመሪያ ይወጣለታል፡፡

11.9. ማንኛውም አባል ለኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ መጠናከርና ለአላማዎቹ መሳካት የመታገል ግዴታ አለበት፡፡

11.10. ማንኛውም አባል የሚኖርበትን ክልልና ሀገሪቱ የምትመራባቸውን ህገ-መንግስትና ሌሎችንም ህጐች የማክበርና እንዲከበሩም የመታገል፣ የህዝቦችን ዴሞክራሲያዊ አንድነትና ደህንነት የሚፈታተን ማንኛውንም የጠላት ጥቃትና ባእዳዊ ወረራ የመከላከል ግዴታ አለበት፡፡

11.11. ማንኛውም አባል ሰፊው የአማራ ህዝብና በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚገኙ ብሔረሰቦች እንዲሁም ሌሎች የአገራችን ህዝቦች በትግላቸው የተቀዳጁዋቸውን ድሎች ከማንኛውም አደጋ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ በአማራውና በሌሎች ህዝቦች መካከል መኖር የሚገባውን ወንድማማችነትና አጋርነት የሚጐዳ ተግባር መፈፀም የለበትም፡፡

11.12. ማንኛውም አባል የብአዴንን፣ የግንባሩንና የወዳጅ ድርጅቶችን ሰነዶችና ምስጢሮች እንዲሁም በተመደበበት የድርጅትና የመንግስት ስራ እንዲጠቀምበት የተሰጠውን ንብረት፣ ሰነድና ምስጢር የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

11.13. ማንኛውም አባል የህዝብን ሃሳብ የማዳመጥ፣ የህዝብን ባህልና እምነት የማክበር፣ ህዝብን አሣምኖ የማሰራት ባህልን የማዳበር ግዴታ አለበት፡፡

11.14. ማንኛውም አባል ድርጅቱ በሚያወጣው ፕሮግራምና በራሱም ተነሳሽነት የፖለቲካ ብቃቱን የማሳደግ፣ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ባህሉንና የሙያ ብቃቱን የማጠናከር፣ ገንቢ የሆነ ሂስና ግለሂስ የማካሄድ፣ ማንኛውንም ዓይነት ኋላቀር ዝንባሌዎችን አጥብቆ የመዋጋት ግዴታ አለበት፡፡

11.15. ማንኛውም አባል የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ መጠበቅ አለበት። አንጃኝነትና ቡድንተኝነት የተከለከለ ነው። የአንጃኝነትና የቡድንተኝነት ዝንባሌና ድርጊት ማጋለጥና መታገል አለበት።

11.16. ማንኛውም አባል ድርጅቱን ከሰርጎ ገብነትና ከጠላት ጥቃት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

11.17. ማንኛውም አባል ሙስናና አድሎአዊ አሰራርን የመከላከል፣ የመታገልና የማጋለጥ ግዴታ አለበት።

## ምዕራፍ ሶስት

## የብአዴን የአደረጃጀትና የአሰራር መርሆዎች

### አንቀፅ 12

### የአደረጃጀት መርሆዎች

12.1. የብአዴን ድርጅታዊ አሰራር በድርጅቱ ውስጥ የአባላትን የሃሳብና የተግባር አንድነት የሚፈጥር፣ የግለሰብ አምባገነንነትና ተክለ ሰውነትን የሚያስወግድ፣ የዲሲፕሊን፣ የስራ ቅልጥፍናና ውጤታማነትን የሚያጠናክር የጋራ አሰራርና አመራር እንዲሁም የግል ኃላፊነት እንዲረጋገጥ በሚያስችሉ መርሆዎች ላይ ይመሰረታል።

12.2. የብአዴን ድርጅታዊ መርሆዎች የአባላት የአላማ ፅናትና የስራ ተነሳሽነት እንዲበለጽግ፣ የአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ፣ በድርጅቱ ውስጥ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያደርጉ ይሆናሉ።

12.3. ብአዴን የተሟላ ውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ እንዲኖር፣ ድርጅታዊ ሁኔታውን በአግባቡ እየገመገመ ድክመቶቹን የሚያስተካክልበትና ጥንካሬዎቹን የሚያጐለብትበት፣ ስህተቶችን የሚያርምበት፣ ገንቢ የመተራረም ስርዓት እንዲጠናከር የሚያደርጉ ድርጅታዊ መርሆዎችን ይጠቀማል።

12.4. የብአዴን ድርጅታዊ መርሆዎች ብዙሀን የወሰኑት በውህዳን ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚያደርጉና ውህዳንም የብዙሃኑን ውሳኔ እየተገበሩ በልዩነታቸው ግን አግባብ ባለው መንገድ ሁሉ የመከራከር መብታቸውን የሚያስከብሩ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 13

## የአመራር አካላት አመሰራረትና አሰራር

13.1. በየደረጃው የሚገኙ የብአዴን አመራር አካላት የሚመሰረቱት በምርጫ ይሆናል። በምርጫ ማቆም በማይቻልበት ሁኔታ በምደባ እንዲከናወን ይደረጋል። ምደባው አንድ እርከን ከፍ ብሎ ባለው መዋቅር ተዘጋጅቶ ቀጥሎ ባለው አካል ከፀደቀ በኋላ ተፈፃሚ ይሆናል።

13.2. በምርጫም ሆነ በምደባ በየደረጃው በሚቋቋሙ የአመራር ኮሚቴዎች ውስጥ ብቃትን መሰረት ባደረገ አኳኋን የሴቶች ተዋፅኦ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሟላ ይደረጋል። ዝርዝር አፈፃፀሙ ማእከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

13.3. በማንኛውም አመራር አካል ውስጥ ሊቀመንበርና እንደ አስፈላጊነቱም ምክትል ሊቀመንበር ይኖራል። የሚመረጡትም ባሉበት ኮሚቴ ይሆናል።

13.4. በየደረጃው የሚኖረው የአመራር አካል በኮሚቴ የሚመራ ይሆናል። በተዋረድ በሚዋቀሩ አካላትና አባላት መካከልም ዴሞክራሲያዊ የሆነ ግንኙነት ይኖራል።

13.5. በየደረጃው ያሉ አመራር አካላት ለበላይ አካላቸው ተጠሪ ይሆናሉ።

13.6. የበታች አካላት ከበላይ አካላቸው የሚሰጣቸውን መመሪያ መተግበር አለባቸው።

13.7. የበላይ አካላት ከበታች አካላት አስተያየት መሰብሰብ፣ ለሚያቀርቡዋቸው ጥያቄዎች በወቅቱ መልስ መስጠት፣ የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ መከታተልና ማወቅ፣ ችግሮቻቸውን መፍታት የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን ማሳየትና ብቁ ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል። ነገር ግን በድጋፍ፣ በክትትልና በቁጥጥር ስም እነሱን ተክተው የሚሰሩበት ሁኔታ መፈጠር የለበትም።

13.8. የበታች አካላት የበላይ አካል ውሳኔንና እቅድን በማይፃረር መንገድ የአካባቢያቸውን ጉዳይ በሚመለከት ውሳኔ ማስተላለፍ፣ እቅድ ማውጣት፣ በውሳኔያቸውና እቅዳቸው መሰረትም መንቀሳቀስ ይችላሉ። ስለስራቸውም ለበላይ አካል ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

13.9. በአንድ አካል የተወሰነን ውሳኔ መሻር የሚችለው ራሱ የወሰነው አካል ወይም የበላይ አካሉ ይሆናል።

13.10. ማንኛውም የአመራር አካል በሚመራው ክልል በሚታዩ ጉድለቶች በሚወስናቸው ውሳኔዎች ላይ እንደ አካል ተጠያቂነት ይኖርበታል።

13.11. በአንድ አካል ውስጥ እንዲሰሩ የተመደቡ አባላት በኮሚቴው ስራ ላይ እኩል ኃላፊነት አላቸው። ለኮሚቴው የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ስራ ላይ መዋላቸውን መከታተልና አስፈላጊ አመራር መስጠት የኮሚቴው አባላት የጋራ ኃላፊነት ነው።

13.12. ለአንድ ኮሚቴ የተሰጠን ምድብ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ለአንድ ሰው ብቻ ማስተላለፍ አይቻልም። ይሁንናም ስራዎችን በስራ ክፍፍል የመስራት አሰራርን ይከተላል። አባላቱም በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት እንደ ኮሚቴ በጋራና ከስራ ክፍፍላቸው አኳያም እንደ ግለሰብ ተጠያቂ ይሆናሉ።

13.13. አንድ የኮሚቴ አባል በሂስ የማይሻሻልና ለኮሚቴው ስራም እንቅፋት ሆኖ ሲገኝ ያለበት ኮሚቴ ከኮሚቴ አባልነቱ ሊያግደው ይችላል። ውሳኔውንም በዝርዝር ሪፖርት ለበላይ አካሉ ማሳወቅ ይኖርበታል። ከኮሚቴ አባልነቱ የሚወገደው ግን ኮሚቴው ተጠሪ በሆነበት የበላይ አካል ይሆናል።

13.14. በድርጅቱ ውስጥ የግልፅነትና የተጠያቂነት አሰራር እንዲጎለብት መደረግ ይኖርበታል። ምስጢር ተብለው ከሚያዙ የተለዩ ጉዳዮች ውጪ የድርጅቱ አቋሞችና መሰረታዊ ውሳኔዎች አግባብ ካለው ማብራሪያ ጋር አባላትና ህዝቡ እንዲያውቃቸው ይደረጋል።

## አንቀፅ 14

## የውሳኔ አሰጣጥ አግባብ

14.1. ማንኛውም አካል ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት በጉዳዩ ላይ በብቁ መረጃ ላይ ተመስርቶ ነፃና በቂ ክርክርና ውይይት ማካሄዱን ማረጋገጥ አለበት። ከአባላቱ ሰፊ ተሳትፎና ክርክር በኋላ የውሳኔ ሃሳቦች ተዘጋጅተው ውሳኔዎችን ወደ መስጠት ይገባል።

14.2. የማንኛውም አካል መደበኛ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ መካሄድ አለበት። በስብሰባው ላይ የሚቀርቡ አጀንዳዎች አስቀድመው ተሰብሳቢዎቹ እንዲያውቋቸው መደረግ ይኖርበታል። እንደሁኔታውም ከስብሰባው ቀደም ብሎ በአጀንዳዎቹ ላይ የመነሻ ፅሁፍ ሊዘረጋ ይገባል።

14.3. ማንኛውም አካል በሚያካሂደው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መያዝ አለበት። ውሳኔዎች በሚገባ ተፅፈው ሊፀድቁና በሰነድ ሊያዙ ይገባል። ውሳኔውን የሰጡ አባላትም በፊርማቸው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

14.4. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተለይተው ከተደነገጉት በስተቀር የማንኛውም የአመራር አካል ምልአተ ጉባኤ ከኮሚቴው አባላት 50%+1 ሲገኙ ነው። በሞት፣ በቅጣት፣ በስንብት ወይም በክዳት በኮሚቴው ውስጥ በቀጣይነት እንደማይገኙ የታወቁ አባላት በምልአተ ጉባኤ ላይ ታሳቢ አይደረጉም። ምልዓተ ጉባኤው የተጓደለውን ቁጥር መነሻ በማድረግ

ይሰራበታል፡፡ ይሁንና ግን ከአንድ የአመራር አካል ከ1/3ኛ በላይ የሚጐድል ከሆነ በፍጥነት የሚተኩበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡

14.5. የአንድን አመራር አካል ምልአተ ጉባኤ እንዳይሟላ ሆን ብሎ ጥረት ማድረግ በዲሲፒሊን ያስጠይቃል፡፡

14.6. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተለይተው ከተደነገጉት በስተቀር በማንኛውም አካል በስብሰባው ከተገኘው ውስጥ የአብላጫ ድምጽ ያገኘ (50%+1) ሃሳብ የአካሉ ውሳኔ ይሆናል፡፡ ድምጽ እኩል በሚሆንበት ወቅት ሊቀመንበሩ የደገፈው የአካሉ ውሳኔ ይሆናል፡፡ የውሳኔውን ሃሳብ የማይቀበሉ ውህዳንም የብዙሃኑን እምነት በተግባር እየተረጎሙ ተቃውሞአቸውን አግባብ ባለው የድርጅት መድረክ ማቅረብና መታገል ይችላሉ፡፡

14.7. በአንድ አካል የተወሰነን ውሳኔ ከተሰብሳቢዎቹ ውስጥ 1/3 /አንድ ሶስተኛ/ ያህሉ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ጥያቄ /ሪኮንሲደሬሽን/ ካቀረቡ ጉዳዩ ለውይይት ክፍት ይሆናል፡፡ የእንደገና ይታይልን ጥያቄው አካሉ በስብሰባ ላይ በሚሆንበት ወቅት በቃል፣ አካሉ ከተበተነ በኋላ ከሆነ ደግሞ በፅሁፍ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በምንም መልኩ ቢሆን ቡድንኛ በሆነ መንገድ ተደራጅቶ የእንደገና ይታይልን ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፡፡

## አንቀፅ 15

## የምርጫዎች አፈፃፀም ሥርዓት

15.1. ማንኛውም አባል ለምርጫ እጩ /ተወዳዳሪ/ ማቅረብ ይችላል፡፡

15.2. በምርጫ ላይ ሁሉም መራጮች እኩል ድምጽ ይኖራቸዋል፡፡

15.3. ማንኛውም አባል ለውድድር የቀረበ እጩ ተመራጭን በሚመለከት ማብራሪያ እንዲሰጠው የመጠየቅ፣ ደግፎ የመከራከር ወይም እንዳይወዳደርም ሆነ እንዳይመረጥ መቃወም ይችላል፡፡

15.4. ማንኛውም ለውድድር የቀረበ እጩ ተመራጭ በምርጫ ሂደቱ የሚቀርብለትን ጥያቄ ሆነ ተቃውሞ ምላሽ የመስጠትና ራሱን የማስተዋወቅ መብት አለው፡፡

15.5. ምርጫዎች የሚካሄዱት ነፃና ቀጥተኛ በሆነ አግባብ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱም በሚስጥር ወይም በግልጽ ይከናዎናል፡፡

15.6. ማንኛውም ለምርጫ የቀረበ ሰው እጩ በመሆን ለውድድር ሊመዘገብ የሚችለው ከተሰብሳቢው የ1/3ኛ /ሲሶ/ ድምጽ ድጋፍ ካገኘ ነው፡፡

15.7. አንድ ተወዳዳሪ ለታጨበት ቦታ ሊመረጥ የሚችለው ከተወዳዳሪዎቹ አብላጫ ድምፅ ሲያገኝ ነው፡፡

15.8. ማንኛውም አባል እጩ ተወዳዳሪዎችን በሚመለከት የሚያቀርበው ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ በሀቅ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት:: ከምርጫ ጋር በተያያዘም ሆነ በሌላ ሁኔታ የተዛባ መረጃ በመስጠት የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ለማድረስ መሞከር ወይም ማድረስ የተከለከለ ነው:: በኃላፊነትም ያስጠይቃል::

## አንቀጽ 16

## የዲስፒሊን፣ ግምገማ፣ ሂስና ግለሂስ ስርዓት

16.1. ማናቸውም አባል ሆነ አካል የድርጅቱን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ፣ ልዩ ልዩ ደንቦች፣መመሪያዎች እንዲሁም የድርጅቱን እቅዶችና ውሳኔዎች የሚያከብር፣ ለሃሳብና ለተግባር አንድነት የሚቆም፣ ራሱን ለድርጅቱ ተልእኮዎች ተገዥ ያደረገ፣ ለህዝብ ታማኝና ህዝብን አክባሪ፣ ከሙስና የተቆጠበ/የፀዳ/፣ በአጠቃላይ በመልካም ስነ-ምግባር ታንፆ የሚጓዝ መሆን ይገባዋል:: በእነዚህ ላይ የሚታይ ጉድለት የዲሲፕሊን ጉድለት ተደርጐ ይወሰዳል::

16.2. መላ የድርጅቱ አካላትና አባላት በእምነትና በፍላጐት ላይ የተመሰረተ የአካላትንና የአባላትን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ዲሲፕሊን አክባሪነትንና አስከባሪነትን በተግባር የመተርጐም አሰራር ይከተላሉ::

16.3. ግምገማ ድርጅታችን ከአዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተሞክሮዎቹ ገንቢ ትምህርት የሚገበይበት፣ ሂስና ግለሂስ በአባላትና አካላት እንዲሁም በአጠቃላይ ድርጅቱ ውስጥ የሚታዩ ስህተቶችን ለማስተካከል ሲባል የሚካሄድ ቋሚ አሰራሮች ናቸው::

16.4. ሁሉም የድርጅት አካላት እቅድ ሲያወጡ በቅድሚያ ያለፈውን እቅድ አፈፃፀም በተገቢው መገምገም ይኖርባቸዋል:: እያንዳንዱ አካል ሥራዎቹን ከገመገመ በኋላ የአባላትን ሂስና ግለሂስ ማካሄድ እንደቋሚ አሰራር መያዝ ያለበት ይሆናል::

16.5. በድርጅቱ ውስጥ የሚካሄዱ ግምገማዎች በተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ፣ ግለሰቦችን ሳይሆን ስራን ማእከል ያደረጉ ሂስና ግለ ሂሶችም በዴሞክራሲያዊ አግባብና ገንቢ በሆነ መንገድ የሚከናወኑ መሆን ይገባቸዋል::

16.6. አባላት፣ አካላትና በአጠቃላይም ድርጅቱ በተሳሳቱባቸው ጉዳዮች ላይ ቅንና አስተማሪ የሆኑ ግለሂሶችን በይፋ መውሰድ አለባቸው:: ሌሎች በሰሩት ስህተትም ላይ ገንቢ ሂስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል:: ከሁሉ በላይ ደግሞ ስህተቶች ከመሰራታቸው በፊት አስቀድሞ መቆጣጠር የሚያስችሉ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ሊኖሩ ይገባል::

## አንቀፅ 17

## ቅጣት

17.1. ቅጣት የድርጅታችንን ብቃትና ጥራት የማረጋገጥና የማጠናከር፣ የአባላትን ፖለቲካዊ ግንባታና ዲስፕሊን የማጎልበት ... አስተማሪና ገንቢ ዓላማ ይኖረዋል፡፡

17.2. በዲሲፕሊን ጉድለት ላይ እንደጉድለቱ ክብደትና ቅለት እየተመዘነ ከቀላል እስከ ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ይሰጣል፡፡

17.3. የቅጣት ዓይነቶች፡-

- 17.3.1. የቃል ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣
- 17.3.2. ለእጩ አባል የእጩነት ጊዜን ማራዘም፣
- 17.3.3. ከእጩ አባልነት መሰረዝ፣
- 17.3.4. ከሙሉ አባል ወደ እጩ አባልነት ማውረድ፣
- 17.3.5. ከኃላፊነት ለተወሰነ ጊዜ ማገድ፣
- 17.3.6. ከኃላፊነት ዝቅ ማድረግ፣
- 17.3.7. ከኃላፊነት ማውረድ ፣
- 17.3.8. ሙሉ አባልን ከአባልነት ለተወሰነ ጊዜ ማገድ፣
- 17.3.9. ከድርጅት ማባረር ናቸው፡፡

17.4. እንደጥፋቱ ሁኔታ በማየት አንድ ዓይነት ቅጣት ወይም የተለያዩ ቅጣቶችን በማጣመር ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

17.5. በድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛው ቅጣት ከድርጅቱ ማባረር ነው፡፡ በማባረር የሚያስቀጡ ጥፋቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

- 17.5.1. ከድርጅቱ የተለየ የፖለቲካ ፕሮግራምና ስትራተጅ ይዞ ይህንኑ በተግባር ለመተርጐም መሞከር፤ የብዙሃን ውሳኔን ተግባራዊ አለማድረግ፣
- 17.5.2. የብዙሃንን ውሳኔ ሆን ብሎ ተግባራዊ አለማድረግና ማደናቀፍ፣
- 17.5.3. የከፋ የስነ ምግባር ጉድለት መፈፀም፣
- 17.5.4. በድርጅቱ ውስጥ ቡድን መፍጠር ወይም አንጃኝነት፣
- 17.5.5. ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ለ6 ወራት የድርጅት ወርሃዊ መዋጮ አለመክፈል፣
- 17.5.6. የድርጅት መርሆዎችን በተደጋጋሚ መጣስ፣
- 17.5.7. በወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት የተፈረደበት፡፡

17.6. ማንኛውም አባል የሚቀርብበትን ክስ የማወቅ፣ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ ካመነ የተጠየቀበትን ጥፋት አልፈፀምኩም ብሎ የመከራከር፣ አለኝ የሚለውን መረጃ የማቅረብ መብት አለው::

17.7. ቅጣት ለተወሰነበት አባል የተፈፀመውን ጥፋት፣ የተወሰነበትን የቅጣት አይነት፣ በዝርዝር የሚገልጽ ጽሑፍ የወሰነው አካል ሊሰጠው ይገባል፤ ይኸው ጽሑፍ ከአባሉ ማህደር ጋር ተያይዞ እንዲቀመጥ ይደረጋል:: ቅጣት የተወሰነበት አባል አስተያየቱን በፅሁፍ በማስፈር ከማህደሩ ጋር እንዲያያዝ የማድረግ መብት አለው::

17.8. በተወሰነበት ቅጣት ላይ ቅሬታ ያለው አባል በድርጅቱ የይግባኝ አሰራር መሰረት ለሚመለከተው አካል አቤቱታ የማቅረብና መልስም የማግኘት መብት አለው::

17.9. ማንኛውም አባል በአንድ አባል ላይ ያለአግባብ ቅጣት ተወስኗል ብሎ ካመነ በድርጅቱ የአሰራር መመሪያ መሰረት ለሚመለከተው አካል ተቃውሞውን ማቅረብ ይችላል::

17.10. ከማባረር በመለስ ባሉ ቅጣቶች የተቀጣን አባል ሁኔታ በየጊዜው መከታተልና ለውጡን በመገምገም ከጥፋቱ መታረሙን ማረጋገጥ፣ ይህንንም በአባሉ ማህደር ላይ እንዲሰፍር ማድረግ ይገባል::

17.11. ከብአዴን አባልነት የተባረረ ሰው በማንኛውም ቦታ ብአዴንን አይወክልም::

17.12. አንድ አባል ያጠፋው ጥፋት መንግስትና ህዝብን የሚመለከት ከሆነ በድርጅቱ ከሚሰጠው የዲሲፕሊን ቅጣት በተጨማሪ ጉዳዩ በመንግስት ህግ እንዲታይ ብአዴን አስፈላጊውን ትግል ያደርጋል::

17.13 በድርጅቱ ውስጥ የሚፈጸሙ ቅጣቶች በማእከላዊ ኮሚቴ በሚወጣ የቅጣት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት የሚመሩ ይሆናል::

## ምዕራፍ አራት

## ድርጅታዊ መዋቅር

## አንቀፅ 18

## ጠቅላላ

18.1. የብአዴን ድርጅታዊ አወቃቀር መልክአ ምድራዊ አከላለልን ወይም የስራ ቦታን የተከተለ ነው::

18.2. የብአዴን ዋነኛ መንቀሳቀሻ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሲሆን ድርጅታዊ መዋቅሩን በክልሉ ውስጥ በሚገኙት የአማራና ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ ይዘረጋል::

18.3. ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ የአማራ፣ የዋግኽምራና አዊ ብሔር/ብሔረሰብ/ ተወላጆችን የሚያደራጅበትና የሚያታግልበት ድርጅታዊ መዋቅርም ይኖረዋል::

18.4. ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ አባላት አደረጃጀትና ስምሪት በኢህአዴግ መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያዎች መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል::

## አንቀጽ 19

## መዋቅራዊ ቅርፅ

19.1. የድርጅቱ ከፍተኛው መሪ አካል ድርጅታዊ ጉባኤ ሲሆን የመጨረሻው ዝቅተኛው አካል ደግሞ ህዋስ ነው::

19.2. እንደ መልከአ-ምድራዊና ወቅታዊ ሁኔታው እየታየ በማእከላዊ ኮሚቴው የሚቋቋሙ የተለያዩ መዋቅሮች ሊኖሩ ቢችሉም የድርጅቱ መደበኛ መዋቅራዊ ቅርፅ የሚከተለው ይሆናል::

- 19.2.1. ድርጅታዊ ጉባኤ
- 19.2.2. ማእከላዊ ኮሚቴ
- 19.2.3. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
- 19.2.4. ማእከላዊ ቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽን
- 19.2.5. የብአዴን ጽ/ቤት
- 19.2.6. የበታች አመራር /የዞንና የወረዳ/ ኮሚቴዎች
- 19.2.7. መሰረታዊ ድርጅት
- 19.2.8. ህዋስ

19.3. የሊግ አደረጃጀት

- 19.3.1. የብአዴን የወጣቶች ሊግ
- 19.3.2. የብአዴን የሴቶች ሊግ

## አንቀፅ 20

## ድርጅታዊ ጉባኤ

**20.1. አመሰራረት**

20.1.1. የብአዴን ድርጅታዊ ጉባኤ ከሁለት እስከ ሁለት ዓመት ተኩል (2-2½ ዓመት) ባለ ጊዜ ውስጥ አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣

20.1.2. ጉባኤውን በመደበኛ ወቅቱ መጥራት የማይቻልበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም ማእከላዊ ኮሚቴ እስከ ስድስት ወር ሊያራዝመው ይችላል:: ሆኖም ጉባኤውን

ከስድስት ወር በላይ ማራዘም አይቻልም:: ስለጉባኤው መራዘም በወቅቱ አባላት እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል::

20.1.3. ድርጅታዊ ጉባኤ በነፃና ዴሞክራሲያዊ መንገድ በተመረጡ የአባላት ተወካዮች ይመሰረታል::

20.1.4. የድርጅታዊ ጉባኤ ምልአተ-ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ከጉባኤተኞች 2/3ኛው ሲገኙ ነው::

20.1.5. በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የጉባኤው ውሳኔዎች በአብላጫ ድምፅ (50%+1) ይወሰናሉ::

**20.2 አስቸኳይ ጉባዔ**

20.2.1. ከማእከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል (50%+1) ድምጽ አስቸኳይ ጉባዔ እንዲካሄድ ከጠየቁ አስቸኳይ ጉባዔ ሊጠራ ይችላል::

20.2.2. አስቸኳይ ጉባኤ መጠራቱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምን አባል ጥያቄውን ላለበት አመራር ኮሚቴ አቅርቦ በ1/3ኛ ድምጽ ማስደገፍና በየደረጃው ለሚገኙ የበላይ አመራር ኮሚቴ እየቀረበ ተመሳሳይ ድምጽ ድጋፍ ካገኘ ማእከላዊ ኮሚቴው የአስቸኳይ ጉባኤውን ጥያቄ ከምክንያቶቹ ጋር ለጉባኤው ቋሚ አባላት በመዘርጋት ከጉባኤው ቋሚ አባላት የ1/3ኛ ድምጽ ድጋፍ ካገኘ አስቸኳይ ጉባኤው እንዲጠራ ያደርጋል:: ማንኛውም አካል በእንደዚህ አግባብ የሚኖርን እንቅስቃሴ የማመቻቸት ኃላፊነት ይኖርበታል::

20.2.3. የማእከላዊ የቁጥጥርና የኦዲት ኮሚሽን በ1/3ኛ ድምጽ አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራ መጠየቅ ይችላል:: ጥያቄውን ለማእከላዊ ኮሚቴ አቅርቦ ተቀባይነትን ካላገኘና በመልሱም ካልረካ ጥያቄውን በቀጥታ ወደ ጉባኤው ቋሚ አባላት በመዘርጋት የ1/3ኛ ድምጽ ድጋፍ ካገኘ አስቸኳይ ጉባኤ ይጠራል::

20.2.4. በአንድ ጉባኤ የተሳተፉ ጉባኤተኞች እስከሚቀጥለው ጉባኤ ድረስ ቋሚ የጉባኤ አባላት ሆነው ይቀጥላሉ:: አስቸኳይ ጉባኤ በሚጠራበት ወቅት ምልአተ ጉባኤውን የሚያዛባ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር አዲስ የጉባኤተኛ ምርጫ አይደረግም:: ቋሚ የጉባኤ አባላቱ አስቸኳይ ጉባኤውን ይመሰርታሉ::

20.2.5. የአስቸኳይ ጉባኤ ምልአተ ጉባኤ ከተሳታፊዎቹ 60% የተገኙበት ይሆናል::

20.2.6. አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ ቢበዛ በሁለት ወር ውስጥ መጠራት ይኖርበታል::

**20.3. የጉባኤው ስልጣንና ኃላፊነት፡-**

20.3.1. የድርጅቱን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ያፀድቃል፣

20.3.2. የድርጅቱን የስትራቴጂና የወቅቱን የታክቲክ መስመሮች ይወስናል፣

20.3.3. የማእከላዊ ኮሚቴንና የማእከላዊ ቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽንን ይመርጣል፣ ይሽራል፣

20.3.4. በማእከላዊ ኮሚቴና በማእከላዊ ቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽን የሚቀርቡትን ዘገባዎች ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔ ይሰጣል፣

20.3.5. ድርጅቱ ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር የሚመሰርታቸውን ግንኙነቶችና የሚገዙበትን መርህ ይወስናል፤ የተፈጠሩ ስምምነቶችን ይገመግማል፣ ያፀድቃል፣ ይሽራል፣

20.3.6. የድርጅቱን  እቅዶች ያፀድቃል፣

20.3.7. ጉባኤው ከጉባኤተኞች በተመረጠ ፕሬዚዲየም ይመራል፡፡

**20.4. የጉባኤ ዝግጅት**

20.4.1. የጉባኤ ዝግጅት በአዘጋጅ ኮሚቴ የሚከናወን ይሆናል፡፡

20.4.2. የመደበኛም ይሁን የአስቸኳይ ጉባኤ ዝግጅት በማዕከላዊ ኮሚቴ በሚቋቋም የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ይመራል፡፡

20.4.3. የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው ቁጥርና ተዋፅኦ በማዕከላዊ ኮሚቴ ይወሰናል፡፡

20.4.4. የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

20.4.4.1. የጉባኤውን ዝግጅት በበላይነት ይመራል፣

20.4.4.2. የጉባኤውን አጀንዳዎች በሚመለከት ከማእከላዊ ኮሚቴና ከመላ አባላቱ ሃሳቦችን ያሰባስባል፤ በአጀንዳዎቹ መሰረትም ዝግጅት እንዲካሄድ ያደርጋል፣

20.4.4.3. የጉባኤ ተሳታፊዎችን ቁጥር፣ ስብጥርና የአወካከል አግባብን በሚመለከት መመሪያ ያዘጋጃል፤ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማፀደቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

20.4.4.4. ጉባኤው የሚሰየምበትን ቀንና ቦታ ይወስናል፣

20.4.4.5. ለጉባኤው አስፈላጊ የሆኑ ሎጅስቲካዊ ዝግጅቶችን ያሟላል፣

20.4.4.6. የጉባኤውን ዝግጅት በሚመለከት ከስራ አስፈፃሚ ጋር በመደጋገፍ ይሰራል፣

20.4.4.7. ለጉባኤው ስለ ስራው ሪፖርት በማቅረብና ፕሬዚዲየም በማስመረጥ ዋነኛ ተግባሩን ያጠናቅቃል፡፡

## አንቀፅ 21

## ማዕከላዊ ኮሚቴ

**21.1. አመሰራረት**

21.1.1. ማእከላዊ ኮሚቴ በቀጥታ በጉባኤ በሚመረጡና ከወጣቶችና ከሴቶች ሊጎች **የብአዴን አባል የሆኑ አመራሮች** በሚወከሉ አባላት ይመሰረታል።

21.1.2. አጠቃላይ የማእከላዊ ኮሚቴው አባላት ብዛትና ስብጥር በጉባኤው ይወሰናል፣

21.2. አሰራር

21.2.1. የማእከላዊ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በየስድስት ወሩ ይደረጋል፣

21.2.2. የማእከላዊ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም ከማእከላዊ ኮሚቴ አባላት 1/3ኛ ከጠየቁ ይጠራል።

**21.3 ስልጣንና ኃላፊነት**

21.3.1. በሁለት ጉባኤዎች መካከል የድርጅቱ የበላይ አመራር አካል ነው፤ ሁሉን አቀፍ ድርጅታዊ ተግባራት፣ ሁሉን አካላትና አባላት በበላይነት ይመራል፤ ተጠሪነቱም ለድርጅታዊ ጉባኤ ይሆናል፣

21.3.2. በሁለት ጉባኤዎች መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ የድርጅቱን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና የጉባኤውን አበይት ውሳኔዎች መተርጐም የሚችል ከፍተኛው የአመራር አካል ነው፣

21.3.3. በጉባኤው የፀደቁትን የድርጅቱን መስመሮች፣ ውሳኔዎችና እቅዶች መሰረት በማድረግ ወቅታዊና አስፈላጊ የሆኑ አቋሞች፣ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችን እያወጣ እቅዶችን እያቀደ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል። ከአዳዲስ ሁኔታዎች ጋር በተዛመደ መያዝ የሚገባቸውን አዳዲስ አቋሞችና ፖሊሲዎች ይነድፋል፤ ያስፈፅማል፣

21.3.4. የብአዴን ወጣቶችና ሴቶች ሊግን እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፣

21.3.5. እንደ ድርጅቱ እድገትና እንደየ አካባቢው ሁኔታ ድርጅቱን ያዋቅራል፣ የነበሩ መዋቅሮችን ያስተካክላል፤ አዳዲስ አወቃቀሮችንም እየነደፈ ይተገብራል፤ እንዲተገበሩም ያደርጋል፤ በአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት በምርጫ የተዋቀሩ አካላት በሚፈርሱበት ሁኔታ አዲስ ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ ጊዜያዊ አካል በመሰየም ያንቀሳቅሳል፣

21.3.6. በተለያየ ምክንያት በማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት መቀጠል በማይገባው አባል ላይ ከኃላፊነት ማገድ፣ ማውረድ ወይም ከድርጅት አባልነት የማባረር ውሳኔ

የመወሰን ስልጣን አለው፤ ውሳኔው ከማእከላዊ ኮሚቴ አባላት በ2/3ኛ ድምጽ መደገፍ ይኖርበታል፤ ውሳኔውን ከነምክንያቱ ለአባላት ያሳውቃል፣

21.3.7. ከማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት ውስጥ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴን፣ የድርጅቱን ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር እንዲሁም የኢህአዴግ ምክር ቤትና የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፤ አስፈላጊ ሲሆንም ይቀይራል፣

21.3.8. ራሱን በተለያዩ ኮሚቴዎች በመመደብ በስራ ክፍፍል ይሰራል፣

21.3.9. ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ድረስ የነበረውን ድርጅታዊ እንቅስቃሴ፣ አገራዊና ክልላዊ ሁኔታውን እንዲሁም የወጣቶችና የሴቶች ሊጎችን እንቅስቃሴ አስመልክቶ ለድርጅታዊ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል።

## አንቀፅ 22
## ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

### 22.1. አመሰራረት

22.1.1. በማእከላዊ ኮሚቴ የሚመረጥ አካል ነው፤ ቁጥሩ በማእከላዊ ኮሚቴ ይወሰናል፣

22.1.2. የወጣቶችና የሴቶች ሊጎች የብአዴን አባል የሆኑ ሊቃነ-መናብርት በቀጥታ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፣

22.1.3. የማእከላዊ ኮሚቴ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይሆናሉ፣

22.1.4. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በ3 ወር አንድ ጊዜ ይደረጋል፣

22.1.5. አስቸኳይ ስብሰባ በሊቀ/መንበሩ ወይም ከአባላቱ አንድ ሶስተኛ (1/3ኛ) ከጠየቁ ሊጠራ ይችላል፣

### 22.2 ስልጣንና ኃላፊነት

22.2.1. ተጠሪነቱ ለማእከላዊ ኮሚቴ ሆኖ በሁለት የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባዎች መሀል ሁሉንም የድርጅቱን ተግባራት፣ አካላትና አባላት በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

22.2.2. በማእከላዊ ኮሚቴ የሚወጡ እቅዶችን፣ ውሳኔዎችንና ፖሊሲዎችን ተግባራዊነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚወሰኑ ወቅታዊ ጉዳዮችንና አቅጣጫዎችን በድርጅት ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣

22.2.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላቱን ጨምሮ የሌሎች ማእከላዊ ኮሚቴ አባላትን ለተለያየ ሥራ ይመድባል፣

22.2.4. የማእከላዊ ኮሚቴውን መደበኛ ስብሰባ ይጠራል፣ የስብሰባውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣

22.2.5. ስለስራው ለማእከላዊ ኮሚቴ ዘገባ ያቀርባል።

## አንቀፅ 23

## የድርጅቱ ሊቀመንበር

23.1. የማእከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል፣

23.2. ተጠሪነቱ ለማእከላዊ ኮሚቴ ሆኖ በሁለት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች መሀል የድርጅቱን አካላትና እንቅስቃሴያቸውን በበላይነት ይመራል፣

23.3. ድርጅቱን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር ይገናኛል፣

23.4. የስራ አስፈፃሚና የማእከላዊ ኮሚቴን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ይጠራል፣

23.5. ስለስራው ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል።

## አንቀፅ 24

## የድርጅቱ ምክትል ሊቀመንበር

24.1. ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ወቅት ሊቀመንበሩን ተክቶ ይሰራል፣

24.2. በማእከላዊ ኮሚቴ፣ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 25

## ማእከላዊ ቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽን

**25.1. አመሰራረት**

25.1.1. ማእከላዊ ቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽን በድርጅታዊ ጉባኤ የሚመረጥ ተጠሪነቱም ለጉባኤ የሆነ አካል ነው፤ ቁጥሩ በጉባኤው ይወሰናል፣

25.1.2. የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ለኮሚሽኑ አባልነት ሊመረጡ አይችሉም፣

25.1.3. ኮሚሽኑ የራሱን ሊቀመንበር ይመርጣል፣

25.1.4. ቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽን ጽህፈት ቤትና ቋሚ ምድብተኛ አባል ይኖረዋል።

**25.2. ስልጣንና ኃላፊነት**

25.2.1. የአባላት መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤ ከአባላት የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች ክሶች ያዳምጣል፤ ጉዳዮችን አጣርቶ መፍትሔ እንዲያገኙ አስተያየቱን ለማእከላዊ ኮሚቴ ያቀርባል፣

25.2.2. የድርጅቱ ሰነዶች፣ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ መያዛቸውን፣ በህጋዊ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤ የሚታዩ ጥፋቶችን አጣርቶ የመፍትሔ ሃሳቦችን ለማእከላዊ ኮሚቴ ያቀርባል፣

25.2.3. ኮሚሽኑ ባሳለፋቸው ውሳኔዎችና የሚያቀርባቸው ሀሳቦችና አስተያየቶች ከማዕከላዊ ኮሚቴ ጋር የሀሳብ አንድነት ከተያዘበት ውሳኔው ተግባራዊ ይሆናል፤ ልዩነት ከተከሰተ ማዕከላዊ ኮሚቴ የሚያሳልፈው ውሳኔ እስከ ጉባኤው ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል፣

25.2.4. በድርጅቱ ውስጥ በማእከላዊ ኮሚቴው ጥረት ብቻ ሊፈቱ ያልቻሉ ችግሮችን እንደ አንድ ነፃ አካል ያጣራል፤ እስከ መደበኛ ጉባኤ ፋታ የሚሰጡ ጉዳዮችን አጣርቶ ሪፖርቱን ለመደበኛ ጉባኤ ያቀርባል፣ አስቸኳይ ጉባኤ የሚያስጠራ ሆኖ ካገኘው ደግሞ በአንቀፅ 20.2.2 መሰረት እንዲጠራ ያደርጋል፣

25.2.5. ከኮሚሽኑ አባላት ውስጥ ጥፋተኛና ለማረም ጥረት ተደርጐም የማይሻሻል ሆኖ ያገኘውን በ2/3ኛ ድምፅ ከኃላፊነት ማገድ ወይም ማውረድ ይችላል፤ ከአባልነት የማባረር ውሳኔ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያ መሰረት ይሆናል፣

25.2.6. በየደረጃው ያሉ የኮሚሽኑ አባላት ሲጓደሉ በምርጫ እንዲተኩ ያደርጋል፣ ይህን ማድረግ በማይቻልበት ሁኔታ ከማዕከላዊ ኮሚቴ ጋር በመመካከር በምደባ እንዲሟሉ ያደርጋል፣

25.2.7. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያወጣል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

25.2.8. የበታች አካላት ሪፖርት ያዳምጣል፤ ለስራው አመቺ ሆኖ ባገኘው መልክ የበታች አካላትን ያዋቅራል፤ ያዋቀራቸውንም ተገቢ ድጋፍ ይሰጣል፣

25.2.9. ስለ ስራው ለጉባኤ ዘገባ ያቀርባል፣

25.2.10. ከኢህአዴግ ቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽን ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ሁኔታ ይኖራል፣

25.2.11. ኮሚሽኑ ከማእከላዊ ኮሚቴ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በድርጅቱ ሊቀመንበር ወይም ሊቀመንበሩ በሚወክለው አካል አማካኝነት ይሆናል።

## አንቀፅ 26

## የብአዴን ጽህፈት ቤት

**26.1. የጽ/ቤቱ አመሰራረት**

26.1.1. ጽ/ቤቱ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚመደብ የአመራር ኮሚቴ ይመራል፣

26.1.2. የአመራር ኮሚቴው ሰብሳቢ የጽ/ቤቱ ሃላፊ ይሆናል፣

26.1.3. የብአዴን ጽ/ቤት ተጠሪነት ለድርጅቱ ሊቀመንበር ነው።

**26.2. የጽ/ቤቱ ተግባርና ሃላፊነት**

26.2.1. የማእከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲሁም የኢህአዴግ ጽ/ቤት እቅዶችንና ውሳኔዎችን መሰረት በማድረግ በህዝቡና በአባላት ውስጥ የሚካሄደውን የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ስራ ያቅዳል፣ ያስፈጽማል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

26.2.2. የድርጅቱን የእቅድ አፈፃፀም ለህዝብ የማስተዋወቅና ከህዝብ የሚመጡ ጥያቄዎችን የማስተናገድ ሃላፊነት ይኖረዋል፣

26.2.3. የድርጅቱን ሰነዶችና ንብረቶች በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

26.2.4. በማእከላዊ ኮሚቴ የሚጸድቀውን የድርጅቱን አመታዊ በጀትና ፋይናንስ ያስተዳድራል፣

26.2.5. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይመራል፣ በዋናው ጽ/ቤትና በየደረጃው ባሉ የድርጅት ጽ/ቤቶች የሚሰራውን የሰው ሀይል ያስተዳድራል፣

26.2.6. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከድርጅቱ ሊቀመንበር በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ድርጅቱን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር ይገናኛል፣ ይዋዋላል፣

26.2.7. በድርጅቱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፡

26.2.8. ስለስራው ለብአዴን ስራ አስፈፃሚ ኮሜቴና ለሊቀመንበሩ እንዲሁም ለኢህአዴግ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

**26.3. የጽ/ቤቱ አሰራር**

26.3.1. የጽ/ቤቱ አመራር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣

26.3.2. የማእከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን የማዘጋጀትና የማስተባበር ስራ ያከናውናል፣

26.3.3. ከኢህአዴግ ጽ/ቤት ጋር የስራ ግንኙነት ይኖረዋል፣

26.3.4. አደረጃጀቱንና አሰራሩን እንዲሁም ተግባርና ሃላፊነቱን በሚመለከት በማእከላዊ ኮሚቴ ተጨማሪ መመሪያ ይወጣለታል፡፡

## አንቀፅ 27

## የበታች አመራር ኮሚቴዎች

27.1. በማእከላዊ ኮሚቴ የሚወሰኑትንና በብአዴን ጽ/ቤት የሚመሩ በየደረጃው የሚከናወኑ የህዝብ ግንኙነትና ድርጅት እንዲሁም የሰው ሃይልና የፋይናንስ ጉዳዮችን የሚያስፈፅሙ የበታች የአመራር ኮሚቴዎች በዞንና በወረዳ ደረጃ ይዋቀራሉ፡፡

27.2. የዞንና የወረዳ አመራር ኮሚቴዎች በአባላት ምርጫ ይሞላሉ፤ ምርጫ ባልተቻለበት ሁኔታ የዞን አመራር ኮሚቴ አባላት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ የወረዳ አመራር ኮሚቴ ደግሞ በብአዴን ጽ/ቤት ይመደባሉ፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ ማእከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

27.3. የዞን አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች አሉት፡፡

27.3.1. ከብአዴን ጽ/ቤት የሚሰጠውን አመራር መሰረት በማድረግ በዞኑ ውስጥ የሚካሄደውን የህዝብ ግንኙትና የድርጅት ስራ ያቅዳል፣ ያስፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

27.3.2. በዞኑ ውስጥ ያለን የድርጅት ፋይናንስና የድርጅት ሰራተኛ ያስተዳድራል፣

27.3.3. በዞኑ ውስጥ ያለውን የወጣትና የሴቶች ሊግ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣

27.3.4. የወረዳ አመራርን እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ ተገቢ ድጋፍ ይሰጣል፣

27.3.5. ከወረዳ የሚመጣለትን ሪፖርት መሰረት በማድረግና የራሱንም ክትትልና መረጃ በመጠቀም በዞኑ ውስጥ ያለውን ድርጅታዊ እንቅስቃሴ የሚመለከት ሪፖርት በወቅቱ ለብአዴን ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

27.4. የወረዳ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

27.4.1. ከዞን አመራር በሚሰጠው አመራር መሰረት በወረዳው ውስጥ የሚኖረውን የህዝብ ግንኙትና የድርጅት ስራ ያቅዳል፣ ያስፈፅማል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

27.4.2. የመሰረታዊ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ተገቢ ድጋፍ ይሰጣል፣

27.4.3. መሰረታዊ ድርጅትና ህዋሳት የሚወያዩበትን ወቅታዊ ጉዳይ ይወስናል፤ አስፈላጊ ማወያያ ማቴሪያሎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣

27.4.4. ከመሰረታዊ ድርጅት የሚቀርብለትንና በራሱ ክትትል ያገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ የመሰረታዊ ድርጅትና የየህዋሳትን እንቅስቃሴ በሚመለከት ለዞን አመራር ሪፖርት ያቀርባል፣

27.5. የዞንና የወረዳ አመራር ኮሚቴዎች አሰራር እንዲሁም ተግባርና ሃላፊነትን በሚመለከት ማእከላዊ ኮሚቴ ተጨማሪ መመሪያ ያወጣል።

## አንቀፅ 28

## መሰረታዊ ድርጅት

**28.1. አመሰራረት**

28.1.1. በአንድ ጠባብ የጂኦግራፊ ክልል ወይም የስራ ቦታ የሚኖሩ አባላት በሙሉ በሚሳተፉበት አኳኋን ይመሰረታል፣

28.1.2. በመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ይመራል።

28.2. የመሰረታዊ ድርጅት አሰራር፣ ተግባርና ሃላፊነት

28.2.1. የመሰረታዊ ድርጅቱ በተመሰረተበት ክልል በህዝቡና በአባላቱ ውስጥ የሚካሄድን የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ስራ ያቅዳል፣ ያስፈጽማል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

28.2.2. በስሩ የተደራጁትን ህዋሳት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ድጋፍ ይሰጣል፣

28.2.3. የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴን ይመርጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም በሌላ ይተካል፣

28.2.4. የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴው የእጩ አባላትን ወደ ሙሉ አባልነት የመሸጋገር ውሳኔ ይሰጣል፣

28.2.5. መደበኛ የስብሰባ ጊዜ ይኖረዋል፣

28.2.6. የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋሳትን እንቅስቃሴ የሚመለከት ሪፖርት ለወረዳ አመራር ያቀርባል፣

28.2.7. የመሰረታዊ ድርጅት አሰራር፣ ተግባርና ሃላፊነትን በሚመለከት ተጨማሪ መመሪያ በማእከላዊ ኮሚቴ ይወጣል።

## አንቀፅ 29
## ህዋሳት

29.1. አመሰራረት

29.1.1. መሰረታዊ ድርጅቱ በተዋቀረበት አካባቢ ያሉ አባላት በመኖሪያ ወይም በስራ ቦታ አመችነት ተመስርተው የሚያቋቁሟቸውና የእለት ከዕለት ስራ የሚከናወንባቸው ዝቅተኞቹ አደረጃጀቶች ናቸው፡፡

29.1.2. በህዋስ አመራር ኮሚቴ ይመራሉ፡፡

29.2. የህዋሳት አሰራር፣ ተግባርና ሃላፊነት

29.2.1. የህዋሳት ተጠሪነት ለመሰረታዊ ድርጅት ነው፣

292.2. የራሳቸውን የልማትና መልካም አስተዳደር እንዲሁም የህዝብ ግንኙትና የድርጅት ስራ እቅድ ያወጣሉ፣ ይፈፅማሉ፣

29.2.3. ተልእኮን መሰረት ያደረጉ የአባላት ግንባታ ያካሂዳሉ፣ የአባላት ፖለቲካዊ ህይወት መገንቢያ መድረኮች በመሆን ይንቀሳቀሳሉ፣

29.2.4. የእያንዳንዱ የህዋስ አባል ማህደር በተሟላ መንገድ እንዲያዝ ያደርጋሉ፣

29.2.5. ድርጅቱን የሚቀላቀሉ እጩ አባላትን ምልመላ ያፀድቃሉ፣

29.2.6. መደበኛ የስብሰባ ጊዜ ይኖራቸዋል፣

29.2.7. ስለ ስራቸው ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

29.3. የህዋሳት ዝርዝር አሰራር፣ ተግባርና ሃላፊነት በሚመለከት ማዕከላዊ ኮሚቴ ተጨማሪ መመሪያ ያወጣል፡፡

## አንቀፅ 30
## የብአዴን ሴቶች ሊግ

30.1 የብአዴን ሴቶች ሊግ አደረጃጀት

30.1.1. የብአዴን ሴቶች ሊግ የብአዴንን ኘሮግራም የተቀበሉና ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማ መሳካት ለመታገል የተዘጋጁ ሴቶች የሚሰባሰቡበት ማህበር ነው፡፡

30.1.2. የብአዴን ሴቶች ሊግ የብአዴን አባላትና የብአዴንን ፕሮግራም የተቀበሉ አባላት ያልሆኑ ሴቶች በጋራ ለሴቶች እኩልነትና ማናቸውንም አይነት አድልዎና የመብት መጣስ ለማስቀረት የሚታገሉበት ማህበር ነው፡፡

30.1.3. የሴቶች ሊግ ከብአዴን ጋር በጥብቅ የተሳሰረ አንድ አካል ሆኖ ይደራጃል፡፡

30.1.4. የሊጉ የድርጅት መዋቅር ከብአዴን አደረጃጀት ጋር ተመሳሳይና በየደረጃው ተጓዳኝ በሆነ አግባብ የተዋቀረ ይሆናል፡፡

30.1.5. ሊጉ እድሜያቸው 18 አመትና በላይ የሆኑ ሴቶች የሚሳተፉበት ይሆናል፤ ከ18 በታች ያሉ የብአዴንን ኘሮግራም የተቀበሉ ወጣት ሴቶች በወጣቶች ሊግ ሊደራጁ ይገባል፡፡ ከ18 አመት በላይ የሆኑና በወጣትነት እድሜ የሚገኙ ሴቶች በወጣቶችና በሴቶች ሊግ ወይም በአንዱ ብቻ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

30.1.6. የሴቶች ሊግ ዝርዝር አደረጃጀት፣ ተግባርና ሃላፊነት እንዲሁም አሰራርን በሚመለከት በራሱ በሊጉ ጉባኤ ላይ ፀድቆ በሚወጣው መተዳደሪያ ደንብ የሚመለስ ይሆናል፡፡

30.2. የብአዴን ሴቶች ሊግ መብቶች

30.2.1. ከብአዴን መርሆዎች በማይፃረር አኳኋን የሚዘጋጅ የሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፣

30.2.2. ሊጉ ከላይ እስከታች የተዘረጋ አመራርና መዋቅር ይኖረዋል፣

30.2.3. ከብአዴን የሚያገኘውን አመራር መነሻ በማድረግ የራሱን እቅድ በማዘጋጀት በነፃ ይንቀሳቀሳል፣

30.2.4. የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ላይ በመመስረት በብአዴን ጉባኤ፣ ማእከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲሁም በየደረጃው በሚኖር የድርጅት አመራር ኮሚቴ ላይ መቀመጫ ይኖረዋል፣

30.2.5. በብአዴን አቋሞችና ውሳኔዎች ላይ አስተያየት የመስጠት፣ ሂስ የማቅረብ መብት አለው፡፡

30.3. የብአዴን ሴቶች ሊግ ግዴታዎች

30.3.1. ለብአዴን ኘሮግራምና አብዮታዊ አላማዎች ተግባራዊነት በፅናት የመታገል ግዴታ አለበት፡፡

30.3.2. የብአዴንን አቋሞችና ውሳኔዎችን ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

30.3.3. የአማራ ሴቶች በትግላቸው ከማናቸውም አይነት ጭቆና እንዲላቀቁ የትግል መሳሪያ ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 31

## የብአዴን ወጣቶች ሊግ

31.1. የብአዴን ወጣቶች ሊግ አደረጃጀት

31.1.1. እድሜያቸው ከ15-29 የሆኑ የብአዴንን ኘሮግራም የተቀበሉና ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማ መሳካት ለመታገል የተዘጋጁ የአማራ ወጣቶች የሚሰባሰቡበት ማህበር ነው::

31.1.2. የብአዴን ወጣት ሊግ የብአዴን አባላት የሆኑ ወይም የብአዴንንና የሊጉን ፕሮግራም የተቀበሉ አባላት ያልሆኑ ወጣቶች በጋራ የሚደራጁበት ማህበር ነው፡፡

31.1.3. የወጣቶች ሊግ ከብአዴን ጋር በጥብቅ የተሳሰረ አንድ አካል ግን ደግሞ የራሱ ነፃነት ያለው ማህበር ሆኖ ይደራጃል::

31.1.4. የሊጉ የድርጅት መዋቅር ከብአዴን አደረጃጀት ጋር ተመሳሳይና በየደረጃው ተንዳኝ በሆነ አግባብ የተዋቀረ ይሆናል::

31.1.5. የብአዴን ወጣቶች ሊግ ዝርዝር አደረጃጀት፣ ተግባርና ሃላፊነት እንዲሁም አሰራርን በሚመለከት በራሱ በሊጉ ጉባኤ ላይ ፀድቆ በሚወጣው መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል::

31.2. የብአዴን ወጣቶች ሊግ መብቶች

31.2.1. ከብአዴን መርሆዎች በማይፃረር መልኩ ሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል::

31.2.2. ሊጉ አመራርና ከላይ እስከታች የተዘረጋ መዋቅር ይኖረዋል::

31.2.3. ከብአዴን የሚያገኘውን አመራር መነሻ በማድረግ የራሱን እቅድ የአፈፃፀም መመሪያ በመያዝ በነፃ ይንቀሳቀሳል::

31.2.4. የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ላይ በመመስረት በብአዴን ጉባኤ፣ ማእከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲሁም በየደረጃው በሚኖር የድርጅት አመራር ኮሚቴ ላይ መቀመጫ እንዲኖረው ይደረጋል::

31.3. የብአዴን ወጣቶች ሊግ ግዴታዎች

31.3.1. ለብአዴን ኘሮግራምና አብዮታዊ አላማዎች ተግባራዊነት በፅናት የመታገል ግዴታ አለበት::

31.3.2. የብአዴንን አቋሞችና ውሳኔዎችን ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል::

31.3.3. የአማራ ወጣቶች ብቁ የአገር ተረካቢ እንዲሆኑና በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብና ተግባር እንዲታነፁ የሚያደርግ መሳሪያ መሆን አለበት::

## ምዕራፍ አምስት

## በብአዴንና በኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ መካከል የሚኖር ግንኙነት

### አንቀፅ 32

ብአዴን ህብረ ብሔራዊ የሆነውን ግንባር /ኢህአዴግን/ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በእምነት በመቀበል በነፃ ውሳኔው የኢህአዴግ አባል የሆነ ብሔራዊ ድርጅት ነው፡፡

### አንቀፅ 33

ብአዴን እንደ የኢህአዴግ አባልነቱ የኢህአዴግን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ያከብራል፣ ኢህአዴግ የሚመራባቸውን መስመሮችና መርሆዎች በእምነት ይቀበላል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑም በፅናት ይታገላል፡፡

### አንቀፅ 34

ብአዴን የኢህአዴግን ውሳኔዎች ያከብራል፣ ከአማራ ብሔራዊ ክልልና ከድርጅታዊ ሁኔታው ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### አንቀፅ 35

ብአዴን በኢህአዴግ ውሳኔዎች ወይም ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ላይ ልዩነት ካለው በኢህአዴግ ህጋዊ መድረኮች ላይ ብቻ ይታገልባቸዋል፡፡

### አንቀፅ 36

ብአዴን ከኢህአዴግ አባልነቱ ለመውጣት ከፈለገ በድርጅታዊ ጉባኤ መወሰን ይኖርበታል፡፡ በኢህአዴግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረትም ሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በጉባኤው ላይ በመገኘትም ሆነ በሌላ አስፈላጊ መድረክ ሁሉ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ መፍቀድ ይኖርበታል፡፡

### አንቀፅ 37

በኢህአዴግ ምክር ቤትም ሆነ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሳተፉ የብአዴን ወኪሎች በሚሰሩበት የኢህአዴግ አደረጃጀት መመሪያና አሰራር መሰረት የመንቀሳቀስ ግዴታ አለባቸው፡፡ በመደበኛ ስብሰባዎች የመገኘት፣ በግል ባመኑበት ጉዳይ ላይ ነፃ አቋም የመውሰድና ድምፅ

የመስጠት፣ ከአንጀኛ አስተሳሰብና ተግባር የመራቅና ተልእኮአቸውን በብቃት የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡ የኢህአዴግ ተቋማዊ አሰራሮች እንዲጠናከሩ ጥረት ማድረግና አካላቱ በአግባቡ እንዲሰሩ በትኩረት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## ማጠቃለያ
### አንቀፅ 38

### መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ ይህንን መተዳደሪያ ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ የተለያዩ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል፡፡

### አንቀፅ 39
### ማሻሻልና መሻር

ከድርጅቱ ጉባኤ በስተቀር ማናቸውም አካል ይህንን መተዳደሪያ ደንብ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሻሻል ወይም መሻር አይችልም፡፡

### አንቀፅ 40
### የፋይናንስ ምንጭ

የድርጅቱ የፋይናንስ ምንጭ ከአባላት መዋጮ ከኢትዮጵያውያን ደጋፊዎች የሚገኝ ድጋፍና እንዲሁም በአገሪቱ የፓርቲ ህግ መሰረት ከሌሎች ገቢዎች የሚገኝ ይሆናል፡፡

### አንቀፅ 41
### አውጭው አካል

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በብአዴን 7ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ተመርምሮና ተመክሮበት ተሻሽሎ የወጣ ነው፡፡

## አንቀፅ 42
## ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ በፊት በብአዴን 6ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ የወጣው የብአዴን መተዳደሪያ ደንብ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

## አንቀፅ 43
## የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የብአዴን መተዳደሪያ ደንብ ከመስከረም 1999 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡